# የመልሱ መልስ ለጀለሶቼ ከሃይሉ የሺወንድም

February 9, 2016

የወልቃይት ባህልና የማንነት ጥያቄ በሚል ርእስ በኢትዮሜዲያ የተለቀቀውን ጽሁፌ ተመርኩዘው አራት ግለሰቦች በኢትዮፎረም ድረገጽ ሰፊ ትችት ሰንዝረዋል። ከትችትም አልፈው የእኔን እና የመላ ቤተሰቤን ስብእና የሚያጎድፍ መሰርተ-ቢስ ፍረጃና ተራ የስድብ ውርጅብኝ አዝንበውብኛል። እኔ ግን ታች ወርጀ መልስ በመስጠት የሌለ ክብር ከማጎናጽፋቸው ዝምታን መርጨ ነበር። ምክንያቱም የሰውን ስብእና መሸንቆር ምን ያህል አስነዋሪና ቀፋፊ እንደሆነ በእነሱ አይቸዋለሁ። ነገር ግን ብዙ ጓደኞች መልስ እንድሰጥበት ስለወተወቱኝከወረደ ቋንቋ ፍጹም በጸዳ መንፈስየበኩሌን ለማካፈል ዝግጁ ነኝ።

የጽሁፉ አቀነባባሪዎች ከአንዱ በቀር ሁሉም የዚያ ትውልድ አባላት ናቸው። እነርሱም አባይ መንግስቱ፣ ቻላቸው አባይና ጎሹ ገብሩ ይባላሉ። የዚያ ትውልድ አዎንታዊና አሉታዊ ገጽታ ምን እንደሆነ ከአንባቢው የሚሰወር አይደለም። የተዋናዮቹ ማንነት ከተገለጸ ዘንዳ አስር ጊዜስማቸውን ከማነሳ፣ ከእንግዲህ ወዲያ በስማቸው ፈንታ ጀለሶቼየሚል መጠሪያ እጠቀማለሁ። በአዲሳባኛ ጓደኞቸ ማለት ነው። በእንግሊዝኛ ደግሞ ቀናተኞች ምቀኞች መጋኞች (jealous) ማለት ነው።

1. ጀለሶቸ እንዲህ ሲሉ ይጀምራሉ፣ "እኒህ ግለሰብ የወ/ሮ አዜብ መስፍን ወንድም (የወ/ሮ አዜብ ምስፍን እናትና የአቶ ኃይሉ እናት እህታማቾች) ሲሆኑ እንዲሁም የትግራይ ነጻ አውጭ ግንባር ባለስልጣን የሆነው የአቶ ፈረደ የሺወንድምና  በካርቱም ሱዳን ውስጥ ስደተኞችን በመጠቆምና በማሳሰር በሰፊው የሚታማው የአቶ ተስፉ የሺወንድም ወንድም እንደሆኑ ይታወቃል።"

በጀ! እኔ እስከማውቀው እስከ አሁን ድረስ የፖለቲካ እምነት በዘር ወይም በደም እንደሚተላለፍ ጥናቱ አያሳይም።አንደኛ ፖለቲካ በቤተሰብ አይተላለፍም። ሁለተኛ የወይዘሮ አዜብ መስፍን ዝምድና በኔ ብቻ የሚወሰን አይደለም። በዳያስፖራም በአገር ቤትም ስፍር ቁጥር የሌላቸው የስጋ ዘመዶች አሏቸው። የኔን ጽሁፍ የተቹሶስቱ ግለሰቦች ራሳቸው የወይዘሮ አዜብ የቅርብ ዘመዶች እንደሆኑ በኢሳት ቴቪ ሲናገሩ ታይተዋል ተሰምተዋል። ስለዚህ ቤተሰብ መሆን ለፍርፋሪ ለቃሚነት ባህርይ እንደማስረጃ ሊቀርብ ከቻለ እነዚህ ሰዎችም የጥቅም ተካፋዮች ናቸው ማለት ነው። ወይስ ይህ በጂን የሚተላለፍ በሽታ የሚሰራው ለእኔ ሲሆን ብቻ ነው?

ዝምድናና አማችነትን አስመልክቶ አንድ የራሴ ገጠመኝ ትዝ አለኝ። በዝምድና ምክንያት የተፈረጅኩት አሁን ብቻ አይደለም ለማለት ነው። አንድ ጓደኛዬ ነው። ትንሽ ቆየት ብሏል። ቦታው አስሎ ከተማ ነው። አንድ ቀን ከጓደናዬ ጋር ከተማ ቆይተን ወደየቤታችን ለመሄድ ልንሰነባበት ስንቃረብ ቆጣ-ቆጣ ማለት ጀመረ።

" አንተ እኮ አትታመንም!" አለኝ

"እንዴት ማለት" ቀና ብየ አየሁት

"የመለስ አማች ነህ አሉ፤"   አለ ከንፈሩን እየነከሰ።

"እናስ?" ኮስተር አልኩኝ

"ተወን ባክህ! ስንት ጊዜ መሞኘት አለ?" ፈጠን እያለ እርምጃውን ወደፊት ቀጠለ።

"ቆይ እንጂ!  ከስራ ውጭ ትርፍ ስዓቴን የማሳልፈው ካንተ ጋር ነው።  ከአንተ የተሰወረ ምን ሚስጥር ኖሮኝ ነው የማልታመነው? ለመሆኑ እኔና አንተ ምን የፖለቲካ ተሳትፎ ኖሮን ነው የመታመንና ያለመታመን ጥያቄ የምታነሳው?" አልኩት።

መልስ ሳይሰጠኝ  መስቀልኛው መንገድ ላይ ደረስን። ሳይጨብጠኝ "ቻው!" ብሎኝ ወደ ቤቱ ከነፈ። እኔም የቅርብ ጓደኛዬ በዚህ ከተጠራጠረኝ  ሌላውስ ምን ይለኝ ይሆን በሚል ሃሳብ እንደተዋጥኩና ቅር እንዳለኝ ወደ ቤቴ አመራሁ።"አዜብ ራሷን ችላ ታግላ የገባች መሆኗን አላወቀም አጅሬው" አልኩኝ በልቤ። ቤት ደረስኩኝ። ሶፋ ላይ ሆኜ የምሽቱን የሶስት ስዓት ወሬ

በቴሌቪዥን እየተከታተልኩ እያለሁ የቤቴ በር ደወል ተሰማ። ጓደኛዬ ነበር። ከፈትኩለትና ገባ። እባክህን ከሚስቴ ጋር ስለተጨቃጨቅን ለዛሬ ብቻ እዚህ ሶፋ ላይ ልተኛ አለኝ። እንደ እድል ሆኖ ነገር መቋጠር አልችልም፤ እረሳለሁ። በጊዜ ስንለያይ ያስቀየመኝን ጭራሽ ረስቶ ትኩረቴ ሁሉ በተከሰተው በጓደኛዬ ችግር ላይ ብቻ ሆነ። ወዲያውኑ ለማስታረቅ ወደ ባለቤቱ ስልክ ደውልኩ። “እባክህን ለዛሬ እዛው ይደር። ባይሆን ቁጣው ትንሽ ይብረድለት። ጧት አብራችሁ ኑና ባንድ ላይ ቁርስ እንበላለን፣ ” ብላኝ በዚሁ ተስማምተን ሶፋው ላይ አነጣጥፌለት ተኛ።

እኔም ቲቪውን እንደከፈትኩለት ወደ መኝታ ቤቴ ገባሁ። በዚያን ወቅት ብሮድባንድ ኢንተርኔት ስርጭት የለ፤ ፌስ ቡክ የለ፣ ፓልቶክ የለ፤ ባጠገቤ የነበረችውን ራድዮ ከፍቸ ቢቢሲ አዳምጨ ልተኛ ስል “አንት እኮ አትታመንም! ” የሚለው ድምጽ ከየት መጣ ሳልለው በድንገት ደወለብኝ። በመቀጠልም ከሶስት ቀን በፊት እናቴ ከኢትዮጵያ በስልክ የነገረችኝ አስፈሪ ወሬ እፊቴ ላይ ድቅን አለብኝ። አንድ ገጠር የሚኖሩ ዘመዳችን ቄስ ናቸው። የወንድማቸው ልጅ በአእምሮ በሽታ ይሰቃይ ስለነበር ጸበል ሊያስጠምቁት ይዘውት ወደ ጎንደር ይመጣሉ። ከእናቴ ቤት ያርፋሉ። አንድ ቀን ወለል ላይ ፍራሽ ተነጥፎላቸው ከተኙበት፣ ሌሊት ላይ በሽተኛው ጎረምሳ ትልቅ ድንጋይ ተሸክሞ ያነሳና የቄሱን ጭንቅላት ይጨፈልቃል። ቤታችን በዋይታና በጩኸት ይናጣል። ቄሱ ሌሊቱ በታክሲ ሆስፒታል ድረስ ተወስደው ቀዶ-ጥገና ሕክምና ተደርጎላቸው ሊተርፉ ቻሉ። እኔም የዚህ አይነቱ አዳጋ ሰለባ እንዳልሆን ሰጋሁ። ጓደናዬ ጭንቅላቱ ልክ እንዳልሆነ በዚያን ሰሞን ታዝቤ ነበር። ከተኛሁበት ጭንቅላቴን ፈጥፍጦ “ወያኔ ገዳይ!” እያለ ሬሳዬ ላይ ቆሞ እንዳይፎክር ፍርሃት አድሮብኝ ስለነበር መተኛት አልቻልኩም። ሰውየው ቤቱ እስኪነቃነቅ ድረስ ሶፋ ላይ ተኝቶ ሲያንኮራፋ እኔ ግን እንቅልፍ ሊወስደኝ አልቻለም።አንድ ሃሳብ መጣልኝ። ይኸውም በሕልሜ እየቃዠሁ ቀንደኛ ተቃዋሚ መሆኔን ማሳወቅ ነበር። ጓደኛዬ አሁንም እንቅልፉን እየለጠጠ ነው። “ወያኔ ገዳይ ነው! ወያኔ ይውደም!” አልኩ ጮክ ብዬ። አልሰማም። ድምጼን ከፍ አድርጌ፣ “ኧረ ያገር ያለህ! ኡኡ! ኡኡ!ኡኡኡ!” ስል ከእንቅልፉ ነቅቶ መገለባበጥ ጀመረ። ቀጠልኩና መፈክሬን አሰማሁት፤ “አገር ሻጩ ወያኔ ይውደም! ወያኔ አገሬን እየሸነሸነ ነው! ወይኔ አፋኝ ነው! ድል ለኢትዮጲያ ህዝብ! ዘራፍ ! አካኪ ዘራፍ!!!” ካልኩ በኋላ ቅዠቴን በዜማ ዘመዘምኩት፣ “ተከብረሽ የኖርሽው ባባቶቻችን ደም፣ ባባቶቻችን ደም፤ እናት ኢትዮጵያ የደፈረሽ ይውደም፣ የደፈረሽ ይውደም።” እስኪነጋ ድረስ የሚበቃውን ያህል የህልም መፍታት የቤት ስራ ሰጥቸው በተራዬ ድብን ያለ እንቅልፍ ተኛሁ።

ጧት ከባለቤቱ ጋር በነበረን ውል መሰረት ተነስተን ወደ ቤቱ እየሄድን እያለን በድንገት ቆም አለ።

‶አንተ ምን ዓይነት ሰው ነህ” አለኝ፣ ፈገግ እያለ።

‶አሮንጋዴ”

‶አትቀልድ! በህልምህ’ኮ መለስን ሙልጭ አርገህ ስትሰድበው ነው ያደርከው” አለ፣ አብየት ውሸት!

‶ማ? እኔ? ሊሆን ይችላልህልም ማስታወስ አልችልም” አልኩ ፈርጠም ብየ

‶በቤተ መንግስት’ኮ ከውጭ ጠላት ይልቅ የቤተሰብ አባል ነው በመሪዎች ላይ በጠላትነት የሚነሳው። አላየህም እንዴ ሳዳም ሁሴንን? የከዱት የራሱ የልጆቹ ባሎች ናቸው። እሱም በተራው አታልሎ አስገብቶ ገደላቸው” አለኝ። አባባሉ ሁሉ ከጥርጣሬ መንጻቱን የሚገልጽ ሆኖ አገኘሁት።

ይህን መላ ተጠቅሜ ጓደኝነታችንን አድገ መተማመን የተሞላበት ጊዜ ለወራት ያክል አብረን አሳለፍን። ያለንበት ጊዜ እንደ ድሮው በፖለቲካ ምክንያት ወንድም ወንድሙን፣ ጓደኛ ጓደኛውን የሚያጠፋበት ጊዜ እንዳልሆነ አጥቸው አይደለም። ህይወት አይጥፋ እንጂ የሰው ስም ግን በከንቱ በቀላሉ የሚጠፋበት ጊዜ ቢኖር አሁን ነው። እስከዚህ ድረስ ርቄ ልሄድ የቻልኩት ጓደኛዬን በአሉባልታ ምክንያት ለማጣት ስላልፈለኩ ነበር። የኋላ-ኋላ ግን ጓደኛዬን ማጣቴ አልቀረም። ወደ አገዛዙ በሚወስደው መንገድ ጉዞውን ለመቀጠል ጊዜ አልፈጀበትም። ራሱ ህፍረት ስለተሰማው እንጃ በበኩሌ የፈለገውን ቢሆን ደንታ አይሰጠኝም። አጻጻፉን የልቦለድ አስመሰልኩት እንጂ በእኔ የደረሰ እውነተኛ ታሪክ ነው። እንዲያውም ሲያቀብጠኝ ለእናቴ ተርኬላት

እንግዶች ወደቤታችን በመጡ ቁጥር ስለ ህልሜ እያወራችላቸው ለረዥም ጊዜ መሳቂያ አድርጋኝ ነበር።

2. አሁንም ጀለሶቸ ይቀጥላሉ፣ “ይህ ባንዳነት ባህሪው የሆነው የሆድ-አደሮቹ ቡድን የሚመራው በወ/ሮ አዜብ መስፍን ሲሆን፣ በእርሷ ገንዘብና ስልጣን ሙሉ ድጋፍና እንክብካቤ የሚደረግለት የአንድ ቤተሰብ ስብስብ ነው።”

ከፍተኛ የወልቃይት የማንነት ጥያቄ አቅራቢ የኮሚቴ አባላት አቤቱታቸውን ለማቅረብ አዲስ አበባ ድረስ መጥተው እያለ በአጋጣሚ መንገድ ላይ ተገናኝተን ነበር። ከእነርሱ ጋር የስራ ግንኙነት ባይኖረኝም በስጋ ዝምድና ምክንያት ታሞ የነበረውን ታናሽ ወንድሜ ለመጠየቅ እምኖርበት ቤት ድረስ አብረውኝ መጥተው ነበር። የእኔን አኗኗር እነሱ በዓይናቸው በብረቱ ስለአዩ ዝርዝር ውስጥ መግባት አያስፈልገኝም። ጀለሶቸ እንደሚሉት በወይዘሮ አዜብ መስፍን ገንዘብና ስልጣን ሙሉ ድጋፍና እንክብካቤ የሚደረግለት የሆድ-አደሮቹ ቡድን አባል እንዳልሆንኩኝ ለመገንዘብ የቻሉ ይመስለኛል። በአንድ ነገር ግን ጀለሶቸ አልተሳሳቱም። እነሱ እንዳሉት በወይዘሮ አዜብ ሙሉ ድጋፍና እንክብካቤ የሚደረግለት የሆድ-አደሮች ቡድን አለ። ይህ ቡድን የሚኖረው በኢትዮጵያ መሬት አይደለም። አውሮፓም አውስትራሊአም አይደለም። ኮሎምበስ ኦሃዮ በአንድ ጨለማ ቦታ ውስጥ ይኖራል። ይህ አደገኛ ቡድን በቋሚነት የሚኖረው በአሉባልታ-አደሮቹ፣ በጥላሸት-ቀቢዎቹ ሶስት የኦሃዮ ቦዘኔዎች ጭንቅላት ውስጥ ነው። አዎን! ጨንቅላታቸው ውስጥ። የእነሱን ጽሁፍ ያነበቡ የኮሚቴው አባላት የእኔን አኗኗር ካዩ በኋላ እንዴት ታዝበዋቸው ይሆን? መጥኔ! እኔ ገና ኢትዮጵያ አገሬ መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገሮች ተርታ ስትሰልፍ ያልፍልኛል እያልኩ፣ እነሱ ከወዲሁ ከባለ ጊዜዎቹ ተርታ አሰልፈውኛል። ያፋቸውን ያርግልኝ እንዳልል እኔ አልፈልግም። ጭንቅላታቸው ውስጥ መግባት አልፈልግም።

አቶ ጎሹ ገብሩና አቶ ቻላቸው አባይ የኢሳት ቴለቪዥን ታዳሚዎች ሆነው ሲቀርቡ አስቀድመው ግልጽ ያደረጉት ነገር የወይዘሮ አዜብ ዘመዶች ቢሆኑም ወይዘሮዋን በደንብ እንደማያውቋቸው ነው። ከዚያም ስለ ወይዘሮ አዜብ ጠባይ በስፋት እየተነተኑ ማውገዝና መወንጀሉን ተያያዙት። ስለማታውቀው ሰው መናገር እንዴት ነው የሚቻለው? ሰለማዋውቁት ሰው ደፍሮ መናገር የተመልካችን የማሰብ ችሎታ ዝቅ ማድረግ አይሆንምን? አሁንም የተረባረቡት እኔ ባቀረብኩት ጽሁፍ ይዘት ላይ ሳይሆን በይበልጥ በእኔ ስብእና ላይ ነው። ከአቶ ቻላቸው ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት ኖሮኝ አያውቅም። እርሳቸው አይተውኝ እንደሆነ እንጅ እኔ በህይወቴ አይቻቸው አላውቅም። በአካልም ሆነ በድምጽ ተገናኝተን ተነጋግረን አናውቅም። ስለማያውቁት ሰው ይህን ያህል እርቀው መሄድ በጣም አስነዋሪ መሆኑ ቢታወቅም፣ የፈጠራ ችሎታቸውንና ድፍረታቸውን ግን አደንቅላቸዋለሁ።

3. ጀለሶቸ ይቀጥሉና እንዲህ ይላሉ፣ “አቶ ኃይሉ የሺወንድም ደግሞ ለረጅም ዘመናት በአውሮፓ ኖርዌይ አገር ነዋሪ የነበሩና ካለፉት ሁለት አመታት ወዲህ ግን ነዋሪነታቸውን በኢትዮጵያ ያደረጉ ሲሆን በቅርቡ ሁለት ሰፋፊ የእርሻ መሬቶች በጋንቤላ ውስጥ እንደተሰጣቸውና አዲስ ባለሃብት ለመሆን እየተሯሯጡ የሚገኙ ናቸው።”

በትግራይ ክልል ልዩ አሰራር መሰረት በደርግ የተወረሱ ቤቶች ለባለቤቶቹ እንዲመለሱ ሲታወጅ፣ የአባቴ በርካታ የከተማ ቤቶች ብቻ ተለይተው እንዳይመለሱ ተደርጎ እንደተወረሱ ቀርተዋል። አባቴን በሽታና እርጅና ተጫጭነውት ወደ አገሩ ሲመለስ፣ የሁመራ መኖሪያ ቤቱ እንዲመለስለት ጠይቆ ማመልከቻው ውድቅ ሆኗል። ከዚያም እንደሌሎቹ አዛውንት ጓደኞቹ መኖሪያውን ጎንደር በማድረግ ትንሽ ቆይቶ ሲሞት ዋልድባ ተቀብሯል። ቦምባያ በተባለው ለም ቦታ የነበረን ሰፊ የእርሻ መሬት ማን እያረሰው እንዳለ ግልጽ ነው። ከሁመራ ሌላ፣ ቆላማው የወልቃይት፣ የጠገዴና የቃብቲያ መሬት በማን ይዞታ እንዳለ የታወቀ ነው። ብዙ ወጣቶች አባቶቻቸውና አያቶቻቸው ያቀኑትን ለም መሬት ሲቀሙ ከአያት ከቅድመ-አያት ሲወርድ ሲዋረድ ያገኙትን የእርሻ ሙያ ጥበብ በስራ ላይ ለማዋል ወደ ሌሎች የኢትዮጵያ ክፍሎች ማለትም ወደ ጋምቤላና ቤንሻንጉል መሄድ ነበረባቸው። እኔም እንደ ሌሎች ወልቃይቴዎች፣ ዲያስፖራዎችን ጨምሮ ክስተቱ ስለሳበኝ ሌላ አማራጭ እንዳጣው ህዝቤ ፊቴን ወደ ጋምበላ አዞርኩኝ። የወልቃይት ወጣቶች በጋምቤላ መሬት በስራ ላይ ተሰማርተው በማይበት ጊዜ ውስጤ በደስታና በኩራት ይሞላል። እነዚህየወልቃይት ወጣቶች የኢትዮጵያ ብሩህ ተስፋ ተምሳሌት ናቸው። ስነምግባራቸውና ታታሪነታቸው ለመላ የኢትዮጵያ ወጣትና ህዝብ አርአያ የሚሆን ነው። በዛሬይቱ ኢትዮጵያ ወጣት ሆኖ ከጫት፣ ከሺሻ፣ እሲጋራ፣ከስካር፣ ከብክነት፣

ከልክስክስነት፣ ከብልግና ነጻ የሆነ ዜጋ ማግኘት ብርቅ ነው። ታዲያ ወልቃይቴዎቹ ከዚህ ሁሉ ዝባዝንኬ ነጻ ስለሆኑ እግዚያብሄር ሙሉ ጤና ሃብትና ብልጽግና እየለገሳቸው አምሮባቸው ይታያሉ።

እርግጥ በዚያው ልክ ደግሞ ወልቃይት ያሉ ወንድሞቻቸው እና እህቶቻቸው ትምህርታቸውን ጨርሰው የስራ እድል ተዘግቶባቸው በችጋር፣ በእርዛትና ከስራ አጥነት ጋር ተያያዥ በሆኑ ሱሶች ተጠምደው በአስከፊ ሁኔታ ላይ ይገኛሉ። በአንድ በኩል እነዚህን ምንዱባንና መከረኞች ለመርዳት እየሞከርኩ በሌላ በኩል ጋምቤላ ውስጥ እንደ እኔ መሬታቸውንና ንብረታቸውን ከተቀሙ ወገኖቼመካከል ተገኝቼ በእርሻው ዘርፍ ብሰማራ ሃጢያቱ ምኑ ላይ ይሆን? እንደ ጀለሶቼ እምነት እውነት እኔ ሙስና ውስጥ ብዘፈቅ ኖሮ መሬት ለማግኘት ሁለት ዓመት አይፈጅብኝም ነበር። ያም ሆኖ ላም አለኝ በሰማይ ነው። ሁለት ሰፋፊ መሬት ያሉት ደግሞ ማጋነንና መዋሸት አመላቸው ስለሆነ ነው። ከተገኘአንዱም ሲበዛብኝ ነው። እኔ አኝዋሃ ዞኑ ሃላፊ ባስገባሁት ልዩ ፕሮጀክት መሰረት እርሻው በሚገኝበት ቀበሌ የሚኖሩ ወጣቶች ስራውን ከእኔ ጋር ሆነው በባለቤትነት ወይም በሽርክነት እንዲመሩ ነው። የመጨረሻው ግቤ ወጣቶቹ ራሳቸውን እንዲችሉ አድርጌ ቀስ-በቀስ ሁሉን ለእነሱ አስረክቤ ከስራውና ከንብረቱ ለመውጣት ነው። የዚህ ዓይነቱ ኢንቨስትመንት (Socially Responsible Investment – SRI) ይባላል። የውጭ ኢንቨስተሮች በሚያደርሱት መፈናቀል ምክንያት የሚከሰተው ችግር በመጠኑም ቢሆን በዚህ ፕሮጀክት አማክኝነት መቋቋም ይቻላል ባይ ነኝ።ሌላው ጥቅሙ ደግሞ ሌሎች ገበሬዎች ይህን ምሳሌ ተከትለው የአገሪቱን ተወላጆች ማእከል ያደረገ ልማት እንዲያካሂዱ መንገድ ይከፍታል የሚል እምነት አለኝ።

4. ጀለሶቼ ይቀጥሉና እንዲህ ይላሉ፣ "ውንጀላ 1. "የወልቃይት ጠገዴ ማህበረሰብ የትግራይን ህዝብ ይንቃል (ዝቅ አድርጎ ይመለከታል)" አውቆ የተኛን ቢቀሰቅሱት አይሰማም። እዚህ ላይ የጽሁፉ ጭብጥ ጠፍቷቸው ሳይሆን ሆን ብለው ነገሮችን በማጣመም የሚፈልጉትን አላማ ለመምታት አቅደው ያደረጉት ነው። የእነ ቆርጦ-ቀጥል አላማ እኔን ባንዳ፣ ራሳቸውን አርበኛ ለማድረግ ነው። እኔን ባንዳ ሳያሰኙ እነሱ አርበኛ መሆን እንደሚችሉ ከቶ አይታያቸውም።እኔ የጻፍኩትን ሙሉ ቃል ላስቀምጥና "የወልቃይት ጠገዴ ማህበረሰብ የትግራይን ህዝብ ይንቃል" የሚለውን እዚሁ አፋልጉኝ። ያገኘ ሽልማት አለው።

"የትግራይ ነጻ አውጭ ግንባር ወልቃይትን ከተቆጣጠረበት ጊዜ ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ ያለውን ታሪክ በዜሮ ብናባዛው፣ የህዝበ-ውሳኔው ውጤት ከትግራይ ጋር መኖር የሚሹ ወልቃይቴዎች በሰፊ ልዩነት ሊያቸነፉ መቻላቸውን ያበስር ነበር። ቆይ ግን፣ እንዴት ሆኖ በዜሮ ይባዛል? እንዴትስ ይረሳል? ህወሓቶችስ መች ረሱ? "ድሮ ሰብ ድዩ ሞይቱ ትግራዋይ (ሰው ነው የሞተው ወይስ ትግሬ) ስትሉን ነበርና፣ ኑ ተገረፉ! ድሮ ሁመራ ላይ አሰርታችሁ ደሞዝ ከልክላችሁናልና ስትኩራሩበት የነበረውን ለም መሬት ለእኛ አስረክባችሁ ጥፉ! አገራችሁን በጦር መሳሪያ ሀይል ለመያዝ ልንገድላችሁ ስንመጣ ውድ ጀግና ታጋዮቻችንን እያነጣጠራችሁ ገድላችሁብናልና፣ ኑ ተረሸኑ!" ድርጊቶቹ ተፈጽመዋል ከተባሉበት ከሰላሳና ከአርባ ዓመታት በኋላ የተረሱ ነገሮች ቢኖሩ የወልቃይት እንግዳ ተቀባይነትና በችግር ጊዜ ደራሽነት ብቻ ናቸው።"

ድርጊቶቹ ተፈጽመዋል ሳይሆን "ድርጊቶቹ ተፈጽመዋል ከተባሉበት ከሰላሳና ከአርባ ዓመታት በኋላ" ነው የሚለው። ድርጊቶቹ ተፈጽመዋል የሚለው ሀወሓት ነው። እኔ አልወጣኝም።

አንድ ምሳሌ እንውሰድ። ሰብ ድዩ ሞይቱ ትግራዋይ (ሰው ነው የሞተው ወይስ ትግሬ) የምትለው ዝነኛ አባባል የመነጨችው ሁመራ ላይ ነው። የተናገረችውም የእኔ ዘመድ ወይዘሮ ሐፀ (የስምና የአባት ስም መጀመሪያ ፊደላት) ነበረች። በጊዜው በመቶዎች የሚቆጥሩ የትግራይ ተወላጆች ስራ ፍለጋ ወደ ሁመራ ይመጡ ነበር። ከጉራጌ ማህበረሰብ ሳይቀር የእርሻ ሰራተኞች በአየር እየተጫኑ ሁመራ ውስጥ ይራገፉ ነበር። የወባ በሽታ መድሃኒት ቢኖርም ሰራተኞቹ ስለ ጤና በቂ ግንዛቤ ስላልነበራቸው በየቀኑ ማለት ይቻላል፣ ሰዎች ይሞቱ ነበር። አብዛኛዎቹ መኖሪያቸው የእርሻ ቦታ ስለነበር ከሁመራው ህብረተሰብ ጋር ማህበራዊ ግንኙነት አልነበራቸውም። ሟቾቹ ዘመድ አዝማድ ስላልነበራቸው ህዝቡ በውዴታና በሰብአዊ ርህራሄ ተነስታቶ ነበር የቅብር ስነ-ስርአት የሚፈጽምላቸው። የሃገሩ ተወላጅ ሲሞት ግን የጎረቤቱና የሟቹ ቤተሰብ ተጽእኖ ስለሚኖር መቅበር ግዴታ ነው። እንደሚመስለኝ የዚህ የውዴታና ግዴታ ጉዳይ ሳይሆን አይቀረም የዚህ ዓይነት ጥያቄ አስበውበት ሳይሆን በግብታዊነት ከወይዘሮ ሐፀ አንደበት ሊወጣ የቻለው። በዚያን ወቅት በጭንቅላታቸው ምን ይካሄድ እንደነበር በውል ለማወቅ ጠንቋይ መቀለብን ይጠይቃል። ግራም

ነፈሰ ቀኝ በከፋትና በንቀት ተነስታተው እንዳልሆነ ለማንም ወልቃይቴ ግልጽ ነው። ህወሓቶችና ተከታዮቻቸው ግን የሴትዮዋን አባባል እያጣመሙ የወልቃይት ህዝብ የትግራይን ህዝብ እንደሚንቅ በማስመሰል ለቂም-በቀል አላማ እየተጠቀሙበት ነበር አሁንም እየተጠቀሙበት ነው። መልእክቱ አሁንም ህዝብ-ለህዝብ ማጋጨቱን አልተውትም ነው።መች ረሱ? የሚለው ሃረግ ይህን መልእክት ለማስተላለፍ የተጠቀምኩበት የአገላለጽ ዘይቤ (rhetorics)ነው።

5. ጀለሶች ይጨምሩና "ለወልቃይት አባት ፍለጋ፡ ከትግሪያዊነት ወደ ኤርትራዊነት መንሸራተት....በአጭሩ ወልቃይት ጠገዴ አባቱን ያውቃል።"
እኔ የወልቃይት ባህል ማለት ቋንቋን ጨምሮ ከብሄረ ትግርኛ ጋር በተለይም ከሐማሴን ትግርኛ ብሄረስብ ጋር እንደሚመሳሰል ለመግለጽ እንጂ አባት ወይም ዘርን ፍለጋ አልነበረም።

6. ከዚያም ወረድ ይሉና "አለቃ ታዬ ወልደማርያም "ከለው ከሳባ ወደ ምዕራብ ወደ ደቡብ ያለ ያማራ የወልቃይት የጠገዴ አባት ነው።"
ጀለሶቸ አለቃ ታዬ የጻፉትን የሚያምኑ ከሆነና ከለው የወልቃይት አባት ከሆነ አባትነቱ ለየኤርትራውያንጭምር ነው ማለት ነው። ምክንያቱም ኤርትራውያን የሚኮሩበት በለው-ከለው የተባለ ታሪካዊ ቦታኤርትራ ሰንዓፈ ውስጥ ይገኛል። ስለሆነም ሳያውቁት ዘራቸውን ፍለጋ ኤርትራ የገቡት እነሱ ናቸው። ዞሮ-ዞሮ ሁሉም የኢትዮጲስ ልጆች እስከሆኑ ድረስ አማራዎችም ሆኑ ትግራዮች፣ ኢትዮጵያውያንም ሆኑ ኤርትራውያን ሁሉም አንድ ዘር ናቸው። የጀለሶች ችግር ግን ዘርና ብሄረሰብን መለየት አይችሉም። በነዚህ ሁለት ነጥቦች ላይ መለስተኛ ግንዛቤ ስላልኝ በሌላ ጊዜ እመለስባቸዋለሁ።
ጀለሶቸ የአለቃ ታዬን ስራና ሌሎች ምንጮችን ማገላበጥ የጀመሩት ሰሞኑን ሳይሆን አይቀርም።ታሪክ መዳሰስ የጀመሩት ያገር ቤቱ የማንነት እንቅስቃሴ በጀመረበት ወቅት መሆኑን የሚያመለክቱ ብዙ የግንዛቤና የመረጃ ክፍተቶች ይታዩባቸዋል። ከዚያ በፊት አቶ አባይ ቀደም ሲል በህወሓት የተገደሉ ወልቃይቴዎችን የስም ዝርዝር በማይንቀሳቀሰው በድን ድረገጻቸውላይ ይለጥፉ ነበር። ከዚህ የዘለለ ምንም ያደረጉት ተግባራዊ አስተዋጽኦ አልነበራችውም። በምርጫ 97 ቅንጅት ገናና በነበረበት ወቅት፣የወልቃይትን ጥያቄ ሳነሳ ጀለሶቸና ሌሎች በትኩሳቱ ሰክረው የነበሩ ኢትዮጵያውያን "እባክህን ተወን! ኢትዮጵያ እየደማች ወልቃይት ወልቃይት አትበልብን!" ነበር ያሉኝ። በአንጻሩ በወልቃይት ህዝብ ላይ ሲደርስ የነበረውን ግፍ ለዓለም በማስተዋወቅ በኩል ብቸኛ ድርሻ የነበረው የኢህአፓ ራድዮ ነው። ብራቮ ፍኖተ ዴሞክራሲ! ለእነዚህ ሶስት ግለሰቦች፣ የተገደሉት ሰዎች አሃዝ እንጂ ስጋ እና ደም ያላቸው፣ ልጆችና ቤተሰብ፤ ወላጅ፣ ወዳጅ ያላቸው አይመስላቸውም።የስም ዝርዝሩ በድረገጻቸው እንደ ሐውልት የተገተረው በተገደሉት ሰዎች ሞት ልባቸው ተነክቶ አይደለም። ለራሳቸው የስልጣን ጥማት ማርኪያ መሳሪያ አድርገው ለመጠቀም ነው። ከስም ዝርዝሩ ውጭ ሌላ ሃሳብ ለማፍለቅም ሆነ ከመሬት ወርደው መረጃ ለማሰብሰብ ፍላጎቱም አቅሙም ችሎታውም የላቸውም።ለጀለሶቸ እስታትስቲክስ ከሆኑት ሰዎች ውስጥ ስለ አንዱ፣ ለውድ አንባቢያን ትንሽ ላካፍል ይፈቀድልኝ።
ባለታሪኩ ማለፊያ ጉዐይ ይባላል። እንደ ታሪክ ምፀት ሆኖ ባለፈው ስርአት የተገደለው የጀግናው ወጣት አርበኛ የአቶ መኮንን በርሄ የእህት ልጅ ነበር። ታሪክ ራሷን ስትደግም ታዬ። ለዚህ እድለቢስ ቤተሰብ ሁለቱ ብሄረሰቦችና ስርአቶቻቸው መጡለት ነው የሚባለው ወይስ መጡበት?
ቦታው ሱዳን ነው። በዚያች የሱዳን መንግስት በሰጠን መንደር ከአንድ የቅርብ ዘመዴ ወጣት ልጅ ጋር በጣም ተቀራርበናል። ከዚያ በፊት እኔ አብዛኛውን እድሜዬ ያሳለፍኩት በጎንደርና አዲስ አበባ ሲሆን እሱ ግን ወልቃይት ተወልዶ እዚያው ያደገና የኖረ ነው። በዚህ ምክንያት የገጠሪቱን ኢትዮጵያ ባህልና ስርአት ይዞ ይደገ ነው። የሱዳን ጸሐይ ስታሽቆለቁልና ሙቀቱ በረድ ሲል ብዛት ያላቸው የሰፈሩ ወጣት ወልቃይቴዎች ወንዝ ዳር ጊዜ የሚያሳልፉበት ወቅት ነው። በፉከራና በሽለላ ከሚያዝናኑኝ ወጣቶች መካከል ዘመዴ የመጀመሪያውን ስፍራ ይይዛል። የኔን ስም ጣልቃ እያስገባ ለእኔ ግጥም እየደረደረ ይፎክርልኛል። አሁንም ከስንትና-ስንት ዓመታት በኋላ በአእምሮየ ስእል ይታየኛል። ከአንበሳ ገዳይ አባቶቹና አያቶቹ የወረሰው ቅርስ ነው። በድፍረቱና በቆራጥነቱ እንዲሁም በስራ ታታሪነቱ በጓደኞቹ ዘንድ አድናቆትን ያተረፈ ጀግና ነው። አሁን ግን ነበር ልበለው። በአንድ ወቅት በኢትዮጵያና በሱዳን ድንበር እየተንቀሳቀሰ በግል ስራው ተሰማርቶ እያለ የህወሓት ታጋዮች ይዘው ያስሩታል።

ይህ ማንም ደፍሮት የማያውቅ ቆፍጣና ወልቃይቴ ኢትዮጵያዊ በህወሓት ታጋዮች እጅ ከገባ በኋላ በጃርት ጉድጓድ ውስጥ አስገብተው በተባይ እንዲበላና ሰውነቱ እንዲተላ አደረጉት። ለብዙ ወራት በጨለማ ጉድጓድ አስረው አሰቃዩት። በመጨረሻ ሲፈቱት ቅስሙ ተሰብሮ፣ ከሰው ውጭ ሆኖ፣ ሰውነቱ ተበላሽቶ እንዳልሆነ ሆኖ ነበር።

ከተፈታ ከአጭር ጊዜ በኋላ ጠብመንጃውን በአንድ መንደር አስቀምጦ አንዲት ሽጉጥ ብቻ ታጥቆ ወደ ሱዳን ከተማ አመራ።በመንገድ ላይ ብዛት ያላቸው እስከጥርሳቸው የታጥቁታጋዮች በሩቅ አይተውት ቁም አሉት። እጁን የሚሰጥ መስሎ ከቀረበ በኋላ ደብቆ በያዛት ኮልት ሽጉጥ ሶስቱን ታጋዮች ከናካላሸናቸው ኢጋደማቸው። የቀሩት ታጋዮች በእሩምታ ተኩሰው ጣሉት። እኔ ገና ልጅ እያለሁ ትዝ ይለኛል፤ የእናቱ ታላቅ ወንድም ጀግናው መኮንን በርሄ፣ ቢትወደድ አዳነ ዋስ ጥራ ዋስ ካላገኘህ ትታሰራለህ ሲሉት በሽጉጥ ደረታቸውን ካቆሰለ በኋላ ሁለተኛዋ የመትረየስ ሽጉጥ ጥይት ስለተጠለፈችበት አንድ ፖሊስ አዛዥ ግንባሩን በጥይት መታው። በመቀጠልም ወታደሮቹ ሰውነቱን በጥይት ወንፊት አድርጉት። በበነገታው ጧት ዛፍ ላይ ሊሰቅሉት ሲሉ ሰውነቱ ተበጣጥሶ ስለነበር አልተቻለም። ገላዉን በቆዳ ጠቅልለው ገበያ ሹላዋ ላይ ከነአልጋው ሲሰቅሉት የቃብቲያ ህዝቡ በፍርሃት ተሸብቦ በሃዘን ተውጦ ትእይንቱን በትካዜ ይመለከት ነበር። በዚያች የተረገመች እለት ልክ ግራዚያኒ የቆሰለ ማግስትና አሰቃቂውን እልቂት ተከትሎ አዲስ አበባ ላይ የሰፈነው የሃዘን፣ የቁጭትና የተስፋ መቁረጥ ድባብ ቃብቲያ አድሕርዲ ላይም ሰፍኖ ነበር። ቢትወደድም ከኮማቸው እንደነቁ በቁጣ "ገደላችሁት? አይ ከፉዎች ናችሁ! ለክፉ ቀን የሚሆነውን ጀግና ለምን ገደላችሁት" ብለው እንዳዘኑ እስከአሁን ድረስ ይነገራል።

ማለፊያ ይህ ሁሉ ግፍ ሲደርስበት ከቤተሰቡ ጋር ወደ አሜሪካ ጠቅልሎ ለምሄድ ያስገባው ማመልከቻ ሂደት በመገባደድ ላይ ነበር። ተራው ሲደርስ ከአሜሪካን ኤምባሲ በሱዳን ጥሪው መጣለት። ሚስትየዋ ከልጆቿ ጋር ኤምባሲ ድረስ ሄዳ ሁኔታውን ስታስረዳ ባልሽ ለመገደሉ ማስረጃ አምጪ ተባለች። ለህወሓት ጽህፈት ቤት በአመለከተችው መሰረት ምን እንዳሳሰባቸው አይታወቅም፣ ሟቹ ከታጋዮች ጋር ተኩስ ሲለዋወጥ እንደሞተ ደብዳቤ ጽፈው ሰጧት። በዚህ መሰረት ባለቤቱና ልጆቹ አሜሪካን አገር ሄዱ።

ማለፊያ ለእኔ ትዝታው የማይረሳኝ፣ ቁመናውና መልኩ ከጊዜ ብዛት የማይደበዝዝብኝ ሳስታውሰው ቁጭትና ሃዘን የሚያፈራርቅብኝ ስጋ ለባሽ ሰው ነው። ለሌሎች ግን በወረቀት ወይም በእስክሪን ላይ በተራ ቁጥሩ አኳያ ተሰልፈው የተቀመጡ ፊደላት ነው።እነዚህን ሶስት የስልጣን ጥመኞች፣ አባይ መንግስቱ፣ ቻላቸው አባይና ጎሹ ገብሩ የወንድሜን የማለፍያን ስም የያዘ ወረቀት በጨረፍታ ሲያዩ የሚታያቸው የስልጣን ኮርቻብቻ ነው።

7. ጀለሶቼ እንደጻፉት፣ "አቶ ኃይሉ አገር ቤት ከመግባታቸው በፊት የትግራይ ነጻ አውጭ ግንባር እንደ ወራሪ ኃይል ይመለከቱ እንደነበርና ወልቃይት ወደ ነበረበት ግዛት ወደ ጎንደር ያለ ድርድር መመለስ እንዳለበትም እንደአቋም በመውሰድ ያስተጋቡ እንደነበር ይታወቃል።"

እዚህ ላይ በተለይ አቶ ጎሹ ልብ ቢሉ ጥሩ ነው! ባይገርማችውአሁንም ልክ እንዳስቀመጡኝ ነው ያለሁት። ድሮም አሁንም ለወደፊቱም አቋሜ አንድ ነው። ወልቃይት ወድነበረችበት ወደ ጎንደር እንድትመለስ ነው ሙሉ ፍላጎቴና ምኞቴ። በጽሁፌም የገለጽኩት ይህንኑን ነው። በፊት ግልጽ እንዳደረግሁት ጎንደሬ ለመሆን አማራ መሆን አይጠበቅብኝም። ስለዚህ በእኔ በኩል የተቀየረ ነገር የለም። እንዲያውም ራሴን የታዘብኩበት አንድ ነገር ቢኖር አቋሜን ከጊዜው ጋር መቀያየር ያለመቻሌ ነው። ድሮ ጀለሶቼ አብዮታዊያን ነበሩ፣ በኋላ ሊብራል ደሞክራቶች ሆኑ፣ አሁን ግን ከነፈሰው ጋር መንፈስ ጀምረዋል። ኢትዩጵያና ኢትዮጵያዊነት ይለምልም ሲባል አሜን ይለምልም በማለት በፌስቡክ ስማቸውን Ethiopia First ብለው ይጠመቃሉ። አንዴ ኢሃፓን ሌላ ጊዜ አርበኞች ግንባርና ግንቦት ሰባትን በመሳሰሉ ሕብረ-ብሄር ድርጅቶች ዙሪያ ሲያንዣብቡ ቆይተው አሁን ደግሞ በብሄር እንግስቃሴ ለመታቀፍ የወልቃይት አማራ ማንነት ባለሟል ለመምሰል ሰሞኑን "ከእኛ በላይ አማራ ለአሳር" እያሉ ብቅ ብለውልናል። ጀለሶቼእንደፈለጉት ሲገለባበጡና ሲለዋወጡ፣ ቁጥራቸው ግንአይለወጥም። እንደ ሶስቱ ስላሶች ሶስትነታቸውን ጠብቀው ሞት እስኪለያያቸው ድረስ ይኖራሉ። ሶስት ብቻ ስለሆኑ ወዲህምተለጠፉ ወዲያ ሚዛን አይደፉም። ከእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ ሆነና ከተንኮለኛነታቸው በተጨማሪ ትምህርት የላቸው፣ የፖለቲካ ንቃት የላቸው፣ ሃብት የላቸው ባዶ! የባዶ ባዶ ናቸው።እየገለጽኳቸው ነው፣ እየሰደብኳቸው አይደለም። ከሁሉም ተቃዋሚ ድርጅቶች ጋር ባላቸው ፖለቲካዊ ንክኪ ምክንያት፣ እነርሱን መቅረብ በእንቅስቃሴው መሪዎች ላይ አኬልዳማወይም ጀሃዳዊ ሃረካት ክፍል ሁለት ሊሰራ ቢሞከር የፊልም

ዳይሬርተሮችን ስራ ቀላል የሚያደርግ ነው። እነሱን በሩቁ መያዝ የህገመንግስቱን ከለላ መንፈግ ለሚሞክሩ ሃይሎች ትልቅ ተግዳሮት ሲሆን፣ እነሱን ማስጠጋት ግን ማንም ሊገታው የማይችለውን ሰላማዊ፣ ህጋዊና ህዝባዊ እንቅስቃሴ ማደናቀፍ ይሆናል።

8. ጀለሶቸ "ሲጀመር ወልቃይት የጎንደር እንጂ የአማራ ሆና አታውቅም" ተብሎ ስለተጻፈው ትችት አቅርበዋል። ከዚያ ቀጥዬ የጻፍኩትን አረፍተነገር ግን ሊያዩት አልፈለጉም። ወልቃይት ወደ አማራ ክልል ገባች ማለት የህወሓት አጋር ድርጅት የሚመራውን ብሄረሰብ ተቀላቀለች ማለት ነው። "ሲጀመር ወልቃይት የጎንደር እንጂ የአማራ አይደለችም" የሚለውአረፍተነገር ጎንደር የትግራይ ነች ወደሚለው ያመራል ብለው በቃል ያጫወቱኝ ሰዎች አሉ። ይህ ግን የአንባቢው አንብቦ የመረዳት ችግር ወይም የእኔ በሚገባ መንገድ የመግለጽ ችሎታ ማነስ ካልሆነ በቀር መልእክቴ ከተቀመጠው ውጭ ድብቅ መልእክት የለውም። ሙሉው አረፍተነገር ለማስቀመጥ፣ "ሲጀመር ወልቃይት የጎንደር እንጂ የአማራ ሆና አታውቅም። ምክንያቱም በኢትዮጵያ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስታት አልነበሩምና።"

ወልቃይት የትግራይ እንዳልሆነች እየተረጋገጠ እንዴት ነው ጎንደር የትግራይ የምትሆነው? ጎንደር የተቆረቆረችው እኮ ወልቃይት ከቀናች ከሺህ ዓመታት በኋላ በአፄ ፋሲል ዘመን ነው።የትግራይ ተወላጆች ለመጀመሪያ ጊዜ በብዛት ጎንደር የገቡት በአፄ ኢዮአስ ዘመን ነው። እነሱም ወታደሮች ነበሩ። የንጉሱ አያት እቴጌ ምንትዋብ ጽጥታ እንዲያስከብሩላቸው ራስ ስሑል ሚካኤልን ከትግራይ ጠርተው ሲያስመጡ አብረው የመጡ ናቸው። በዚያን ወቅት ጎንደር ውስጥ ከትግራዮች ይልቅ የኦሮሞዎች ቁጥር ይበዛ ነበር።

9. ጀለሶቸ፣"ጉደኛው ፀሃፊ 'በሁመራ ዘመናዊ እርሻ ምክንያት ሲገኝ የነበረው ገቢ ለደብረታቦር ትምህርት ቤት' " መስሪያና ለሌሎች አካባቢዎች ጥቅም ይውል ነበር። አሁን እንደሚደረገው ማለት ነው" ይሉናል።

የጀለሶቸ ክርክር የሁመራ እርሻ ልማት በ 1950 ዎቹ ጀምሮ በበ 1969 ስለቆመ፣ በዚህ ዚዜ ውስጥ በደብረታቡር ትምህርት ቤት ስላልተሰራ ተሳስተሃል እያሉ ነው። የአንድ ትምህርት ቤት ፕሮጀክት ተቀርጾ ፈንዱ ተገኝቶ ህንጻው ተሰርቶ ስራ እስኪጀምር ድረስ ዓመታት እንደሚፈጅ አይገባቸውም። ለነገሩ አይፈረድባቸውም። ከየት ያመጡታል? ለማንኛውም ወደ ቁምነገሩ። ዳግማዊ አፄ ቴዎድሮስ ትምህርት ቤት በደርግ ይመረቅ እንጂ ስራው የተጀመረው በግርማዊነታቸው ዘመን ነው። ዋቢ ካስፈለገ ምንጩ ሁመራ የሆነ መረጃ አለኝ። ለጊዜው ግን ይህን ዩ አር ኤል ከፍታችሁ ተመልከቱ፣–
https://en.wikipedia.org/wiki/Tewodros_II_Secondary_SchoolTewodros II Secondary School is a comprehensive four-year public high school enrolling more than 4000 students in grades 9 through 12. The school opened in the fall of 1967 and graduated its first senior class in the spring of 1971.Tewodros II Secondary School is accredited by Ethiopian Ministry of Education starting from the reign of Haile Selassie I.

10. ፀሃፊው ውንጀላውን በመቀጠልም "በደጃዝማች አያሌው ብሩ ግዛት ዘመን በወገራ ደጋማና ቆላማ አካባቢ የሚኖሩ አማራዎች በወልቃይት ላይ ወረራዎችና ዝርፊያዎች እንዲያካሂዱ ተደርጓል።" ይሉናል።

ችግሩ እኔን በራሳቸው መለኪያና መነጽር እያዩኝ ነው። እኔ ነጻ ሰው ነኝ። ነጻ ሆኘ በህሊናዬ የማድር ሰው ነኝ። ህሊናዬ ደግሞ የሰው ልጅ ሰብአዊ ሙብቱ ተገፎ፣ ፍትህ ተጓድሎበት፣ ተበድሎ፣ ተገፍቶ፣ በችጋር ተቆራምዶ፣ ማየት አይፈቅድልኝም። የጽሁፌ መንፈስ ህወሓትን በጥፋቶቹ መቃወም ብቻ ሳይሆን፣ ሳልጨምር ሳልቀንስእውነታውን ለአንባቢ ማሳወቅ ነው። እኔን ተቃውመው የጻፉ ግለሰቦች ግን የፖለቲካ ድርጅቶችን በቲፎዞነት ወይም በደጋፊነት የሚያገለግሉ ናቸው። ስለሆነም ምንም ሃቅ ቢሆን የሚደግፉትን ድርጅት የሚነካ ከሆነ እውነት እንደተንካች አድርገው በውሸት ሸንጣቸውን ገትረው ይከላከላሉ።

"እንደሚታወቀው የፊውዳሉ ስራአት" ይላሉ ጀለሶቸ "አንድን ለስርአቱ አልገዛ ወይም አልገብር ያለን ወረዳ ለመቅጣትና ለማስገበር ይጠቀምበት የነበረው አይነተኛ ዘዴ ሌላውን አጎራባች ወረዳ እንዲዘምትበትና እንዲወረው ብሎም እንዲያስገብረው በማድረግ ነበር።" ጀለሶቸ ምን እያሉ ነው? በባላባት ስርአት የተፈጸመ ግፍ በከበርቴ ስርአትም ይሁን በሶሻሊስት ስርአት ከተፈጸመው ግፍ በምን ይለያል። የኦሮሞ ህዝብ እንደ ባሪያ ሲሸጥ የነበረው እኮ "ለስርአቱ አልገዛ ወይም አልገብር" ስላለ እንጂ ሌላ ወንጀል አልፈጸመም። እና በእነሱ እይታ በኦሮሞ ህዝብ የደረሰውን ግፍ ከታሪክ ማሕደር መሰረዝ አለብን ማለት ነው። እንዴት ይረሳል? የወጋስ ይርሳ የተወጋ ግን ይቅር ለእግዚአብሄር ማለት እንጂ መርሳት አይጠበቅበትም።

11. አቶ ሃይሉ “ምዝበራው አልበቃ ብሎ አባወራውን አባርረው ሚስቲቱ አስገድዶ መድፈር የተለመደ ነበር” ይላሉ።የወልቃይት ጠገዴ ማህበረሰብ እንኳንስ በሚስቱና በዕርስቱ ለመጣበት ይቅርና በዋዛ በፈዛዛ ክብሩን ለነካ ሁሉ ምላሹ ጥይት እንደሆነ ጠላታችን ህወሃት ሳይቀር ጠንቅቆ ያውቃል።”

ዋጋ የሌለው ባዶ ድንፋታ ቢቀርባቸውስ። አቶ አባይ መንግስቱ በአንድ የውጭ ራዲዮ፣ ትግራዮች የወልቃይት ወንዶችን አባርረው ሴቶቹን ሁሉ ስለሚይያስወልዱ የእህቴ ልጅ እንጂ የወንድሜ ልጅ የምለው የለኝም ብለው ነበር። ታዲያ “የወልቃይት ጠገዴ ማህበረሰብ እንኳንስ በሚስቱና በዕርስቱ ለመጣበት ይቅርና በዋዛ በፈዛዛ ክብሩን ለነካ ሁሉ ምላሹ ጥይት” ከሆነ እንዴት ማስረገዙና ማስወለዱ ሊቀጥል ቻለ? ወይስ ምላሹን ጥይት ከኦሃዮ እስኪመጣ ድረስ እንጠብቅ? የሃይል ማዘን የሚባል ነገር አለ፣ ጀለሴ። ምንም ጀግና ብትሆን፣ ለባለ ጊዜ የሚያጋድል። ሆኖም ለሁሉም መጨረሻ አለው። ከሰላሳ ምናምን አመታት ሰቆቃ በኋላ ምላሹ ጊዜውን ጠብቆ ራሱ በገዛጁ የመጣ ይመስላል። ይህ ግን ድልን አያመለክትም። ምክንያቱም የነባራዊ ሁኔታው መብሰልና ለፍሬ መቃረብ በባለቤታዊ ማለት በተመጣጣኝ ድርጅታዊ አመራር ካልታጀበና ካልተመራ እንቅስቃሴው ሊኮላሽ ይችላል። ሊያኮላሹት ከሚችሉት አንዱና ዋናው የወልቃይት ህዝብ በጥቃቅኑ ምክንያት መከፋፈል ነው። ስለዚህ መከፋፈልን መዋጋት ማለት ድሉን ወደ ጫፍ ማድረስ ማለት ነው።

12. “ለመሆኑ የትኛው ወልቃይቴ ወይም ጠገድቼ ነው ከወራሪ ወታደር የተወለደና አባቱን የማያውቅ? ... የልጅ ለጆቹስ እነማን ይሆኑ? እንግዲህ መልሱን ለእነ አቶ ሃይሉ የሺ ወንድም እንተዋለን።”

ግዴታ መመለስ ካለብኝ እሺ! መልሱ ቀላል ነው። እኔ ምንጊዜም ድፍን ወልቃይት እንደሚያውቀው አባቴን ስለምመስል እኔ ልሆን አልችልም። የአርበኛው አባቴ ምስል በፌስ ቡክ ተለቅቆ ስለነበር ማወዳደር ትችላላችሁ። ዘር ከልጓም ይስባል እንደሚባለው እንግዲህ ማን በዘር ልጓም እንደተሳበ አንባቢው ይፍረድ።

13. “በስደት የሚገኙት የወልቃይት ጠገዴ ተወላጆች በአሁኑ ሰዓት በሀገር የተቀጣጠለውና የአማራ ምንነት እንቅስቃሴ የሚመሩ ወገኖችን አጀንዳውን ያገኙት የተሰጣቸው ከዲያስፖራው ነው የሚል ሲሆን፤”

በስማም! እግዚኦ ውሸት!ነጭ ውሸት! ያልተጻፈውን እንደተጻፈ በማስመሰል እኔን ከወገኖቸ ለመነጠል የፈበረኩት ነው።

14. “የወልቃይት አማራ ማንነት እንቅስቃሴ በአጭር ጊዜ ተደማጭነት ያገኘው ... የብአዴንን ቡራኬ ስላገኘ ” በማለት የወገናችንን የዘመናት ትግልና መስዋዕትነት ውጤት የሆነውን ይህን ታላቅ ድል እራሱን እንኳ ከህወሃት ቁንጥጫ ማዳን ለማይቻለው የብአዴን ባርኮት ያደርጉታል።“

ይኸኛው ደግሞ ነጭ ውሸት ሳይሆን ማጣመም ይባላል። ጀለሶቸ! የብአዴንን ቡራኬ ስላገኘ ብሎስ ምን ይላል? ምን አለፋኝ? እኔ የጻፍኩትን እስቲ አንብባችሁ ጉዳቸውን እዩልኝ፣

“አማራ ነን የሚሉ የወልቃይት ተወላጆች፣ ደጋፊዎቻቸውና ወኪሎቻቸው በህዝቡ ዘንድ በአጭር ጊዜ ውስጥ ተደማጭነትን ያገኙት በሁለቱ ክልሎች መካከል በወሰን ውዝግብና በቅማንቶች ጥያቄ ዙሪያ በተፈጠረው አለመግባባት ምክንያት የብአዴንን ቡራኬ ስላገኘ ብቻ ሳይሆን፣ የህወሀት ባለስልጣናት የህዝቡን እሮሮ ለመስማት ጆሮ ዳባ ልበስ በማለታቸውና የተሳሳተ ፖሊሲና አያያዝ በመከተላቸው፣ ህዝቡ በጣም ቆስሎ ስለቆየ ጭምር ነው።”

15. ወልቃይትን ከጠገዴ መነጠል
“ወረራውና ዘመቻው እንደ ባህል ሆኖ፣ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በጠገዴው ተወላጅ በክቡር ቢትወደድ አዳነ መኮንን አስተዳደር ሳይቀር በየምክንያቱ ተመሳሳይ ዘመቻዎች።” ይለናል።

ጠገዴ ሌላ ቢትወደድ ሌላ። ስለጠገዴ ይቆይልንና ስለ ክቡር ቢትወደድ አዳነ ትንሽ ልበል። ለምን ዳባት ወይም ጠገዴ አልተቀበሩም የሚለውን መመለስ አያስፈልገኝም። ቢሆንም ቢትወደድ በደማቸውና በአጥንታቸው ኢትዮጵያ ነጻንቷን ጠብቃ የኖረች አገር እንድትሆን በማድረጋቸው ኮርተን እንኖራልን። የታሪክ ቅርስ የሆኑትን ዜጋ ለሞት ያበቃቸው ጀለሶች የነበሩበት ድርጅት ነው። ሲያስተዳድሩት በነበረው አገር እንዳይቀበሩ መደረጉ የህዝቡን ውለታቢስነት የሚያሳይ ነው። በዚህ አንጻር ሲታይ መንግስቱ ሃይለማሪያም ልክ ነበር፣ “የኢትዮጵያ ህዝብ ወርቅ ቢያነጥፉለት ፋንድያ ነው ይላል።” ያለው።እዚህ ላይ አንዴ ልናዘዝ። አያቴ የደጃዝማች ጎሹ ልጅ ደጃዝማች ጎላ ጎሹ በጣም ቅን እና ሰው አማኝ ሰው ነበሩ ይባላል። እርሳቸው በህዝቡ ከባድ ተማጽኖና በመስቀልና በታቦት የታጀበ ልመና ምክንያት ጣሊያን ይዟት የነበረችውን ወልቃይት ለማስተዳደር ሳይወዱ ቢስማሙም ልባቸው ከአርበኞች ጋር ነበር። በቢትወደድ አዳነ በተመራው የጠገዴ ሰራዊትና በደጃዝማች ጎላ በተመራው

የወልቃይት ሰራዊት መካከል ደም እንዳይፋሰስ በማሰብ አያቴ ወደ እርቁ መድረክ ብዙ ተጉዘዋል። ይህን ሲያደርጉ የወልቃይት ሰራዊት በጣሊያን ጦር መሳሪያ እስከ አፍንጫው የታጠቀ መሆኑንና ወታደራዊ የበላይነት እንዳላቸው እያወቁ ነበር። ደጃዝማች ጎላ የደጃዝማች አዳነን (በኋላ ቢትወደድ)ተንኮል ስላልተገነዘቡ ምሽቱን በሙሉ "በጠገዴ ሰዎች ላይ የተኮሰ በጫንቃዬ ላይ እንደተኮሰ እቆጥረዋለሁ" እያሉ ራሳቸው እየዞሩ የሰላም መልእክቱን ሲያስተላልፉ ነበር። የመኝታ ስአት ሲደርስ ግን ከተኙበት ከበው ገደሏቸው። እኔ ይህን ታሪክ ስሰማ ስላደግሁ በልጅነቴ እራሴን አንድ ቀን ቢትወደድን የመግደል የህይወት ተልእኮ እንዳለኝ ሰው እቆጥር ነበር። ከዚያ መማር መጣ። አንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ተገባደደ። ዩኒቨርሲቲ ተገባ። የተማሪ ንቅናቄ መጣ። ማርክስዝም ሌኒኒዝም እንደ ጉድ ተነበበ (እንደ ጀለሶቸ ላይ-ላዩን ሳይሆን)። ነገሮችን በወቅቱ በሰፈነውስርአት አንፃር እንጂ በግለሰቦች ምኞትና ፍላጎት እንዳልሆነ ግንዛቤ ተገኘ። ቢትወደድን እንደ ግለሰብ ሳይሆን በሰፈነው የፊውዶ ቡርዥዋ ስርአራት አገልጋይነት አንጻር መመልከት ተጀመረ። በቢትወደድ ላይ በቀል የመፈጸሙ ተልእኮ እንደ ጉም መብነን ጀመረ። ጃንሆይ ወረዱ – ደርግ መጣ – እኔ ወደ ሱዳን – ቢትወደድም ሱዳን። እሳቸው ኢዲዩ ሆነው በዚያ እድሚያቸው ደርግን ለመውጋት ዘመቱ ማለት የወልቃይቴዎችን ደም እየመለሱ ነበር ማለት ነው። ጀለሶቼ ገፋፍተው ለሞት የዳረጓቸውን፣ የእነ አስፋወሰን ትርፌንና የእነ አንዳርጋቸው አያልነህን ደም፣ እየመለሱልኝ ነበር።ሁኔታዎች ተደማምረው ወደ ይቅር ባይነት አለም ባልገባ ኖሮ እንደ መኮንን በርሄ በደረታቸው ባይሆንም ውጊያ ላይ በጀርባቸው ጥይት ለመልቀቅ ምቹ ሁኔታ ተፈጥሮልኝ ነበር። በዚህ ወቅት ግን በድልድዩ ስር ብዙ ውሃ ፈሷል። ተቀራርበናል።

ይቅር ለእግዚያብሄር ብዬ እርሳቸውን ከመጉዳት ወደ መውደድ በተሸጋገርኩበት ወቅት ከትከሻዬ ትልቅ ሸክም እንደወረደልኝ ተሰማኝ። ግን ምን ታደርገዋለህ! ዞሮ ዞሮ የጀለሶቸ ጓዶች ቢትወደን ገደሉ። ቢትወደድ አዳነ ጀግናው ወጣት አርበኛ መኮንን በርሄ ሲገደል ለክፉ ቀን የሚሆን ጀግና ገደላችሁ ብለው ሃዘን በተሞላበት አንደበት እንደተቆጡ ሁሉ እኔም የጀለሶቸ ጓዶች ቢትወደድን በመግደላቸው ታሪክን እንደገደሉ ቆጥሬ አምርሬ አዘንኩባቸው። ቢትወደድ ቢሞቱም ታሪካቸው ግን አይሞትም። ጀለሶቸ የሌለኝን ስም በመስጠት ጀርባየን በጩቤ ለመውጋት ሊሞክሩ ይችላሉ። የክቡር ቢትወደድን ክቡር ህይወት እንዳጠፉ ሁሉ፣ ንጹህ ስሜን ማጥፋት ይችላሉ። ጥላሸት ከመቀባት ባለፈ እኔን ለመጉዳት ድፍረቱም፣ ወኔውም፣ ችሎታውም፣ቁራጥነቱም፣አቅሙም፣ የላቸውም።

16. የሆድ – አደሮቹ አጀንዳ

"የወልቃይት አማራ ማንነት ኮሚቴ አባላትና ደጋፊዎቻቸው ከተመደበላቸው ስራ ጎን ለጎን ለስታተስ ኮ አንቲ ቅድመ ሁኔታ መሳካት ትርጉም ያለው ጥረት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል።" በማለት ከ 7 ገፅ በላይ በመፃፍ ለከሰሱትና ለወነጀሉት ታጋይ ህዝብና ኮሚቴ የራሳቸውን አጀንዳ ሊጭኑበት ይሞክራሉ።

በእኔ እይታ እንደ መፍትሄ ስታተስኮ አንቲንየመሰለ ግሩም አማራጭ ያለ አይመስለኝም። የዚህ ሃሳብ ችግር ከመልእክቱ ሳይሆን ከመልእክተኛው ነው። የመፍትሄ ሃሳቡ በእነሱ የቀረበ ቢሆን ኖሮ ቻላቸው እራሱ ዜማና ግጥም አውጥቶ ሁመራ እያለ አይባባም አይባባም ሆዴ እያለ ሲያንጎራጉር ነበር እንደተባለው የስታተስኮ አንቲ አልበም በቅርቡ ይለቅልን ነበር። በኢትዮጵያ ፖለቲካ የዚህ ዓይነቱ ችግር ጎልቶ ይታያል። አንዱ ያመጣውን አዲስ ቆንጆ ሃሳብ ሌላው እንዳይበር ክንፉን ይሰብረዋል። ስለዚህ ስታተስኮ አንቲ ሁሉን ወልቃይቴ ሊያሳትፍ የሚችል ግልጽና አጭር መሳሪያ ነው። ሃሳቡ ለሁሉም የሚገባ ነው። ሁሉን አሳታፊ ነው። ለመጫን ሳይሆን ምክር ነው። ጀለሶቸ እንደሚሉት ሌላውን የመጫን ውክልና የለኝም።

17. ጀለሶቸ ስለ ቋንቋ እንዲህ ይላሉ፣ ይልቁንም የወልቃይት ጠገዴና ጠለምት መዘጋዎች ጥጥ ስለሚያመርት ብዙ የትግራይ ተወላጆች በጥጥ ለቀማ ወቅት በየዓመቱ ወደነዚህ መዚጋዎች ይመጣሉ። ዐማሮች ከእነርሱ ጋር ለመግባባት ሲሉ ትግርኛውን ይጠቀሙበታል። ከእንግዶች መካከል ሀገሬውን አግብተው የሚቀሩም አይጠፉም።

ጉድ በል ወልቃይት! ጉድ በል ጎንደር! ትግርኛችን የጥጥ ለቃሚ ትግርኛ ነው ተባለ። አንታ ድርቃኻትኩም ስምዑላይ! ይላል ያገሬ ሰው። በመጀመሪያ ቃል ነበረ፣ ቃልም በእግዚአብሄር ዘንድ ነበረ፣ ቃልም እግዚያብሄር ነበረ። ዮሐንስ ወንጌል 1:1. መጀመሪያ ጥጥ ነበረ፣ ጥጥም በትግሬ ዘንድ ነበረ፣ ጥጥም ትግሬ ነበረ። ጥጥ ለቃሚው ትግሬም ለጥጥ አስለቃሚው አማራ እንዲህ አለው። እውነት እውነት እልሃለሁ ትግርኛ ካልተናገርክ ጥጥህ አይለቀምም ማዳበሪያም አታገኝም። የጀለሶቸ ወንጌ/ጀል

ምእራፍ 666 ቁጥር 666.

ከ ገጽ 12 እስከ 15 ያለው ዝባዝንኬ ስለ እኔው ጽሁፍ ስላልሆነ ትቸዋለሁ።

አቶ ጎሹ ገብሩ

በአቶ ጎሹ ጽሁፍ ላይ ጊዜ ማባከን አያስፈልግም።

*አቶ ጎሹ ገብሩ በሌሎቹ ግፊት ከአራቱ የጽሑፉ አዘጋጅዎች አንዱ እንደሆኑ ተደርጎ ስማቸው ተጨምሯል። ከትንሽ ቆይታ በኋላ በአቶ አባይና በአቶ ቻላቸው ተገፋፍተውም ይሁን እኔን የማዋረድ ሃገራዊ ሚናቸውን ለመወጣት፣የወልቃይት ባህልና ማንነት = መልስ ለአቶ ሃይሉ የሺወንድምበሚል ርእስየበኩላቸውን ፎነጫጭረዋል። ጽሑፉ ከጓዶቻቸው የተኮረጀ ነው። "እጅ በጥፊ ለመምታት እንጂ ለመጻፍ አልተፈጠረም" የሚል ፍልስፍና እንዳላቸው አጻጻፋቸው ያሳብቃል። ለመጻፍ ያነሳሳቸው የከማን-አንሽ በሽታ ጉዳይ ይሁን የውጭ ግፊት በውል አይታወቅም። እነ አቶ አባይ በአቶ ጎሹ ላይ የዝቅተኛነት ስሜት ለማሳደር ይሞክሩ እንደነበር በተለያዩ መድረኮች ለመታዘብ ችያለሁ። አቶ አባይና አቶ ቻላቸው ሆን-ብለው ሃቁን ለመጠምዘዝ የፈለጉበት ምክንያት በማንነት ሙብት እንቅስቃሴ መሪዎችና ደጋፊዎቻቸውዘንድ ተቀባይነትና ርካሽ ዝናን ለማትረፍ መሆኑ አቶ ጎሹ የገባቸው አይመስልም። በእነ ቻላቸውና አባይ እይታአቶ ጎሹ በአንድ ፓርቲ ብቻ ታቅፈው ለረዥም ጊዜ መቆየታቸው እንደ ድክመት የሚቆጠር ነው። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን ሶስቱም የፖለቲካውን ውቂያኖስ እየተገለባበጡ ለመቅዘፍ ቃል-ኪዳን የገቡ ይመስላሉ።*

*ማጠቃለያ*

ሶስቱም ጀለሶቼ ህወሓት ያለ ውጣ-ውረድ ወልቃይትን በወርቅ ሰፌድ እንካችሁ የሚልበት ወቅት የደረሰ ስለመሰላቸው የአስራ አንደኛዋ ስአት የድል አጥቢያ አርበኞች ለመሆን እየጣሩ ነው። ያለ አንዳች መስዋእትነት የድሉ ፍሬ ተቋዳሽ ለመሆን ደፋ-ቀና ሲሉ ይታያሉ። በስልጣን ማማ ለመቆናጥጥ በቋመጡበት ወቅት፣ የእኔ መጣጥፍ ብቅ ስትልላቸው ሎተሪ የደረሳቸው ያህል ሳይፈነድቁ አልቀሩም። እንደ ህንድ ኮብራ ተምዘግዝገው መጣጥፏ ላይ ጉብ አሉ። አስራ ዘጠኝ ገጽ ሙሉ መርዛቸውን ወደ እኔ ረጭተው አይሞቱ ሞት ሊያስጎነጩኝ ሞከሩ። የፖለቲካ ሞት። ለምን ግን? የዚያ ትውልድ ዲያብሎሳዊ ገጽታ በእነርሱ እየተገለጸ ነዋ! ያ ትውልድ ሁለት ተቃራኒ ባህርያት ነበሩት። አንዱ ክርስቶሳዊ ፍቅርና መስዋእትነት ሲሆን ሌላው ሰይጣናዊ አጥፍቶ-ጠፊ ነው። ጀለሶቼ የሰይጣኑ ገጽታ አልጋ ወራሾች ናቸው። በእነሱ ዓለም ድል የሚገኘው በሌላው ሰው መቃብር መቆም ሲቻል ብቻ ነው። የዜሮ ድምር ፖለቲከኞች ባህርይ ይኸው ነው። የእኔን ስም በማጥፋት ይበልጥ ለእንቅስቃሴው ተቆርቋሪ መምሰል የዚሁ እንቅስቃሴውን የመቆጣጠር የመጀመሪያው የተቀናጀ እርምጃቸው ነው። ላለፉት ሰላሳ አምስት ዓመታት ጠብ የሚል ውጤት ሳያመጡ ቆይተው አሁን የወልቃይት ህዝብ ምርር ብሎት በተነሳበት ወቅት ከእንቅልፋቸው ባንነው አዛኝ ቅቤ አንጓች ይሆኑብናል። ላም ባልዋለበት ኩበት ለቀማ እንዲሉ ከመጣጥፌ የሆኑ ፈጠራዎችን እያመጡ አንባቢን ለማደናገር የተቻላቸውን ሞክረዋል።

የኢትዮጵያ ዳያስፖራ ማህበረሰብ በኢትዮጵያ ለሚደረገው ሰላማዊ ትግል በዲፕሎማሲና በመዋእለ ነዋይ በኩል ድጋፍ ማድረግ እንደሚችል ግልጽ ነው። እእነዚህ ከላይ የተጠቀሱት ግለሰቦች (ጎሹ ገብሩ አባይ መንግስቱና ቻላቸው አባይ) በሰፊው የወልቃይት ዲያስፖራ ማህበረሰብ ዘንድ ተሰሚነት የሌላቸውና የተገለሉ ናቸው። ማንም በኮሎምበስ ኦሃዮ የሚኖር ወልቃይቴ ቢጠየቅ ሊመሰክረው የሚችል ሃቅ ነው። አባይ መንግስቱና ጎሹ ገብሩ በዚያ በክፉ ቀን ኢህአፓን ጥለው የሸሹ ናቸው። አባይ መንግስቱ ኢህአፓን መርቶ ወደ ወልቃይት በገባበት ወቅት በህዝቡ ላይ ሲፈጽማቸው በነበረው ጥሰቶችና ወንጀሎች ምክንያት ድርጅቱ በወልቃይቴዎች ዘንድ ጥሩ ስም አላተረፈም። ስለሆነም ህዝቡን ሰብስቦ ገቢ የማሰባሰብ እድላቸው በጣም ዝቅተኛ ስለሆነና የፋይናንስ እርዳታ የመለገስ ችሎታቸው አልቦ ስለሆነ ለእንቅስቃሴው የሚያበረክቱት አስተዋጽኦ ኔፐ ነው።

ስለጀለሶቼ እዚህ ላይ ይብቃኝ። እፎይ!!!

የእኔ መልእክት ወልቃይቴዎች አማራ ባይሆኑም በአማራ ክልል ውስጥ የመኖር መብታቸው የተጠበቀ መሆን አለበት ነው። አማራም ትግሬም አይደለሁም፣ ወልቃይቴ ነኝ ማለት፣ እውነታውን በትክክል የሚያንጸባርቅ ቢሆንም፣ለእኔ ምንም ማለት አይደለም። እኔ ሰው ነኝ ብሎ እንደማወጅ ነው። ጥያቄው ግን እና ምን ይሁን ነው?እና ምን ይሁንማ፣ እኔ በወልቃይቴነቴ

ተበደልኩ፣ ከፋኝ፣ በቃኝ፣ ምናልባት የነበርኩበት የኢትዮጵያ ክፍል – ጎንደር ሳይሻለኝ አይቀርምና ቻው መሄዴ ነው እያለ ነው። ህዝቡ። አስቡ! እንድሄድ ፍቀዱልኝ አይደለም። ህገመንግስቱ ቀደም ሲል ስለፈቀደ ፈቃድ መጠየቅ አያስፈልግም። ይህን ሂደት የሚያደናቅፍ አካል ብቻ ነው ህገመንግስቱን የሚቃረነው።

በአማራነቴ ተጨኮንኩኝ ማለትና በወልቃይቴነቴ ተጨቆንኩኝ ማለት ልዩነትም ግንኙነትም አላቸው። ከቋንቋ ውጭ ዋናው ልዩነት፣ወልቃይቴ ያልተጨቆነበት የወልቃይት ምድር የለም። ወልቃይቴ ራሱን በራሱ የሚያስተዳድርበት የወልቃይት መሬት የለም። ወልቃይቴ ለም መሬቱን ያልተቀማበት የወልቃይት መሬት የለም። በአማራነቴ ይህ ሁሉ ግፍና ሰቆቃ ደረሰብኝ ለማለት ግን አያስኬድም። የወሎ የሰሜን ሸዋ የጎንደር አማራ ራሱን እያስተዳደረ ነው። መሬቱ አልተወሰደበትም። በአገሩ እንደ ሁለተኛ ዜጋ አልታየም። ትግራዮች አያስተዳድሩትም። ስለዚህ አማራ ነን ለሚሉ ወልቃይቴዎች ምናልባት ሊያስኬድ የሚችለው አማራ ስለሆንን ከአማራ ጋር እንቀላቀል ነው እንጂ በአማራነታችን ተጨቁነናል ማለት ውሃ አይቋጥርም።

እዚህ ላይ ትግራይ ነን የሚሉትን ወልቃይቴዎች ለጊዜው እንርሳቸውና አማራ ነን የሚሉትና ብሄረ ወልቃይት ነን የሚሉት የወልቃይት ተወላጆች የሚገናኙት የት ላይ ነው? የሚገናኙት የሁለቱም መዳረሻ የሆነው ጎንደር ነው።ብሄረ ወልቃይት ለብቻው መሆን የሚችለው ወይም የሚፈልገው አንድም ጎንደሮች አማራ ነን ካላላልችሁ አትምጡብን ካሉ ነው። አለያም ከተቀላቀሉ በኋላ የአማራ ክልላዊ መንግስት ባለስልጣናት በተራቸው እንደ ትግራዮቹ ግፍ ከፈጸሙባቸውብቻ ነው።ወልቃይቴዎች ብሄረ ወልቃይት መሆናቸውን በአግባቡ ሳያስረግጡ አማራ ነን ብለውዘው ብለውከተቀላቀሉአሁን ቁጭ ብለው የሰቀሉት ብቅል ቆመውማውረድ ይቸግራቸዋል። ወጣም ወረደ፣ መዳረሻው ጎንደር እስከሆነ ድረስ፣ የትም ፍጪው ዱቄቱን አምጪው ነውና፣ በአማራነታቸው የሚያምኑ ወልቃይቴዎች እውነት ህገመንግስቱ ተተግብሮ ህዝቡን ካለበት አጣብቂኝ ማላቀቅ እንደሚችሉ ከታመነበት ሁሉም ወልቃይቴዎች በጎናቸው መሰለፍ ይኖርባቸዋል። ትግራይ ነን የሚሉትም ጭምር።

ከአሁን በፊት ስለ ወልቃይቴዎች ማንነት የቻልኩትን አበርክቻለሁ። አሁን ስለራሴ ማንነት ልግለጽ።የማንነትን ጉዳይ ህገመንግስቱ ስለአመጣው፣ ህገመንግስቱን ደግሞ ጊዜው ስለአመጣው እንጂ እኔ በበኩሌ ከሁሉ ከሁሉ ከሁሉ በፊት ኢትዮጵያዊ ነኝ። ማንነቴ ኢትዮጵያዊ፣ ዜግነቴም ኢትዮጵያዊ። በትውልድ ወልቃይቴ ነኝ። አማራ/ትግሬ አይደለሁም።የትም ብኖር ቀብራራ ጎንደሬነቴን ማንም አይቀማኝም።

ቲሩ! ቲሩ ላላ!

Hailu Yeshiwondim

Email: hailuyes@gmail.com